ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

የካቲት 2003 ዓ.ም. *የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች* ቁጥር 29

# የአርሶ አደሩ ኢኮኖሚያዊ ጥረት ስኬትና ድህነት ቅነሳ የቡሬ ወረዳ ሞዴል ገበሬዎች ተሞክሮ

*የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡*

*የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡*

*በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡*

*በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡*

*በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡*

## *መግቢያ*

በኢትዮጵያ ድህነትን መቀነስ የመንግስት ዋና አጀንዳ ሆኖአል፡፡ ለዚህም የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ ይህ በብዛት በአነስተኛ አርሶአደሮች የተያዘውን ኢኮኖሚ ምርታማነት ማሳደግ ለአገሪቱ ከሚያበረክተው ከፍተኛ የሥራ ዕድል፣ ከሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪና ከአገሪቱ ጠቅላላ ምርት ውስጥ ከሚሸፍነው መጠን አንፃር ለነገ የሚተው ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው የግብርና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አስፈጻሚ የሆኑት የልማት ሠራተኞች ሞዴል አርሶአደሮችን በመጠቀም አርሶአደሮች የአዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ እያበረታቱ የሚገኙት፡፡ እነዚህ አርሶአደሮች ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ ችሎታቸውን (አንተርፕረነርሺፕ) በማዳበር በራሳቸው ተነሳሽነት አዳዲስ ቴክኖሎጂ በመጠቀምና ምርታማነታቸውን በማሳደግና ኑሮአቸውንም በማሻሻል ለሌሎች አርሶአደሮች አርአያ በመሆን ለድህነት ቅነሳው አጋዥ ኃይል እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ይህን ጥናት በ2003 ዓ/ም ያካሄደው ሞዴል አርሶአደሮች ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ እንቅስቃሴ (በአንተርፕረነርሺፕ) ዙሪያ ያላቸውን ልምድ በመቃኘት ለሌሎች አርሶአደሮች የሚኖረውን ልማታዊ ፋይዳ ለመለየትና በዘርፉ ለሚኖረው ፖሊሲ ግብአት እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡

በግብርና ኤክስቴንሽን ዘርፍ ታታሪና ውጤታማ አርሶአደሮችን እንደ ሞዴል በመጠቀም ሌሎች አርሶአደሮች አዳዲስ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ የማነሳሳት ዘዴ ረጅም ታሪክ ያለው ነው፡፡ የአረንጓዴ አብዮት እየተባለ የሚታወቀው የግብርና ኤክስቴንሽን በደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮች (ለምሳሌ ህንድ፣ ፓኪስታን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ወዘተ) ሲተገበር ሞዴል አርሶአደሮች ቴክኖሎጂን በማስተላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በእኛም አገር በ1960ዎቹ በአርሲና በሌሎች የተወሰኑ አካባቢዎች የአረንጓዴውን አብዮት ቴክኖሎጂ ለአርሶአደሩ ለማስተዋወቅ የተካሄዱት ፕሮጀክቶች በቴክኖሎጂ አስተላላፊነት ተጠቅመዋል፡፡ በደርግም ጊዜ የተካሄዱት የግብርና ኤክስቴንሽን ኘሮግራሞች በወቅቱ ከነበረው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ጋር በማቆራኘት የግለሰብ ሞዴልነት ሳይሆን የእርሻ የሕብረት ሥራ ማህበራት ሞዴልነት ትኩረት ተሰጥቶት የእርሻ ግባአቶችም ሆነ ብድር በቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሞዴል አርሶአደሮች በግብርና ኤክስቴንሽን ያላቸው ጉልህ ድርሻ በስፋት በአገራችን እየታወቀ የመጣው እ.ኤ.አ. በ1995 አዲሱ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሞዴል አርሶአደሮች በግብርና ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ የጐላ በመሆኑ የልማት ሠራተኛው ውጤታማነት የሚለካው ሞዴል አርሶአደሮችንና የእነሱን ተከታዮች በየቀበሌው በቁጥር ከማበራከት ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ለዚህም ነው ይህ ጥናት እነዚህን አነስተኛ፤ ነገር ግን ወሳኝ ሚና ያላቸውን የአርሶአደር ክፍል የሚያሳድሩትን ልማታዊ ተጽዕኖ ትኩረት ሰጥቶ መረጃ በመሰብሰብ ለመቃኘት የተነሳው፡፡

## የጥናቱ ዓላማና መረጃ አሰባሰብ ስልት

የዚህ ጥናት አላማ ለሞዴል አርሶአደሮች ስኬታማነት (ማለትም የግብርና ምርታቸው መጨመር ለገቢያቸው ማደግና ለኑሮአቸው መሻሻል) አስተዋጽኦ ያደረጉትን ሁኔታዎች በመለየት በሌሎች አርሶአደሮች ላይ የሚኖራቸውን አዎንታዊ ድርሻ በመለየት ይህም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ድህነትን ለመቀነስ ለሚካሄደው እንቅስቃሴ የሚኖረውን ፋይዳ ለመመርመር ነው፡፡ በተለይም ጥናቱ በሞዴል አርሶአደሮች የግል፣ ቤተሰባዊ፣ ማህበረሰባዊና አካባቢያዊ የተፈጥሮ ሁኔታዎች ዙሪያ በማተኮር በአገር አቀፍም ሆነ በክልል የተተገበሩ የግብርና ፖሊሲዎች የአርሶአደሩን ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ ችሎታ (አንተርፕረነርሺፕ) ለማበረታታት የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ በመረጃ ላይ ተመስርቶ ይፈትሻል፡፡ እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን የተጠቀመ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም፡-

ሀ/ ከራሳቸው ከሞዴል አርሶአደሮች ጋር ለስኬታማነታቸው ምክንያት በሆኑ ነጥቦች ዙሪያ ጥልቅ ውይይት ማድረግ፤

ለ/ በሞዴል አርሶአደሮችና ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ ሥራ (በአንተርኘረነርሽኘ) ዙሪያ ከልማት ሠራተኞች፣ ከቀበሌ ሥራ አስኪያጆች፣

ከወረዳ ግብርና ባለሙያዎችና የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ባለሙያዎች ጋር ሰፋ ያለ ውይይት ማድረግ፤

ሐ/ ሞዴል ካልሆኑ አርሶአደሮች ጋር የቡድን ውይይት ማድረግ፤ ሌሎች አርሶአደሮች ስለሞዴል አርሶአደሮች ያላቸውን አመለካከት መቃኘት፣ እንዲሁም ሞዴል አርሶ አደሮች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ለውጥን የማነቃቃት ሚናና አስተዋጽኦ መፈተሽ፡- ናቸው::

ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው አብይ ጉዳይ የጥናቱ ዋና ስልት በናሙና ላይ የተመሠረተ አሃዛዊ መረጃ በመሰብሰብ ትንተና ማድረግ ሳይሆን ከሞዴል አርሶአደሮች ጋር ፊት ለፊት በመገናኘትና ጥልቅ ውይይት በማድረግ ስለስኬታቸው፣ ስለአጋጠሟቸው መሰናክሎችና እንዴት እንደተወጧቸው ዘርዘር ያለ ትንታኔ መስጠት ነው::

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ጐጃም ዞን በቡሬ ወረዳ ሲሆን ሦስት ቀበሌዎችን (አንድ የደጋ፣ አንድ የወይና ደጋና አንድ የቆላ) በናሙናነት በመምረጥ ነው:: ቡሬ የኤክስቴንሽን ግብአቶችን በከፍተኛ ሁኔታ የመጠቀም ልምድ ያለው ወረዳ ሲሆን ሞዴል አርሶአደሮችም በኢኮኖሚያዊ የፈጠራ እንቅስቃሴ (በአንተርኘረነርሽኘ) ከፍተኛ ተሳትፎ አላቸው:: ሦስት የተለያየ ስነምህዳራዊ ባህርይ (አግሮኢኮሎጂ) ያላቸው ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት ይህ ስነምህዳራዊው ሁኔታ በሞዴል አርሶአደሮችና በሚያደርጉት ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (አንተርፕረነርሺፕ) እንቅስቃሴያቸው ላይ የሚኖረውን አዎንታዊና አሉታዊ ጐኖች ለመዳሰስ እንዲያመች ነው::

# የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

## በአርሶአደሩ ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች

***ግለሰባዊ ሁኔታዎች፡-*** የአርሶአደሮችን ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (የአንተርፕረነርሺፕ) እንቅስቃሴ በማገዝ ረገድ ግለሰባዊ ሁኔታዎች በጥናቱ ዋነኛ ሆነው ተገኝተዋል:: ከነዚህ ውስጥም ከግለሰቡ ባህሪ ጋር የተያያዙት የመጀመሪያዎቹ ሲሆኑ፤ እነኚህም የግብርና ቴክኖሎጂን ቀድሞ መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ፤ በእርሻ ስራም ሆነ ከእርሻ ውጭ ያሉ የስራና ገንዘብ የማግኛ እድሎችን ቀድሞ መለየትና መጠቀም፤ ጠንካራ የሆነ የተወዳዳሪነት ስሜት፤ አርቆ ማሰብና የወደፊቱን ማቀድን ያካትታሉ::

*ከስራ ልምድ ጋር የሚመነጩ ችሎታዎች፡-* ከነኚህ ውስጥ በመጀመሪያ የሚጠቀሰው መሰረታዊ የሆነ የማስተዳደር ችሎታ ሲሆን፤ ይህም ሞዴል አርሶ አደሮች በሚያሳዩት የላቀ የሰው ሀይል (ተቀጣሪንም ሆነ የቤተሰብ አባላትን) አስተዳደር ይንፀባረቃል:: ሌላው ለሞዴል አርሶ አደሮች ስኬት ምክንያት ሆኖ የተገኘው እቅድ ማውጣትና ላቀዱት እቅድ ተገዢ ሆኖ መገኘትም ነው:: በመጨረሻ የሚገኘው መሰረታዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ነው:: በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት ሞዴል አርሶ አደሮች ውስጥ አብዛኞቹ ወጭና ገቢያቸውን በጥንቃቄ የሚመዘግቡ ሲሆን፤ ይህም ለስራቸው ስኬት በእጅጉ እንደረዳቸው ተናግረዋል::

የእነኚህ ችሎታዎች ምንጮች የቶቹ እንደሆኑ ለማወቅ ጥናቱ ሙከራ አድርጓል:: የዚህም ውጤት ሶስት ዋና ዋና ምንጮችን ያሳያል:: በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ሞዴል አርሶ አደሮች መደበኛ ትምህርት መማራቸውን ከላይ ለተጠቀሱት ችሎታዎች መዳበር እንደምንጭነት ያቀረቡ ሲሆን፤ ይህ ሀሳብም በሌሎች የማህበረሰቡ አባላትና በግብርና ልማት ባለሙያዎችም ተደጋግሞ ተጠቅሷል:: በሁለተኛነት የተነሳው የልምድ ምንጭ ደግሞ በሌሎች ስኬታማ በሆኑ አርሶ አደሮች ስር ቀንጅ ገብቶ መስራት (ማለትም ጉልበቱን ብቻ ይዞ ገብቶ ከምርቱ ላይ በመቶኛ መካፈል) ነው:: ከሞዴል አርሶ አደሮች ጋር የተደረጉ ቃለመጠይቆች እንዳሳዩት ቀንጅ ገብቶ መስራት ከመተዳደሪያነቱ ባለፈ እንደሥልጠና ጊዜ ሊቆጠር እንደሚችል ነው:: አስተዳደግ ሌላው የጠቃሚ ችሎታዎች ምንጭ ሆኖ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ከአባቶቻቸው የወረሱት የተከማቸ ልምድና እውቀት ለስኬታቸው ዋና ምንጭ እንደሆኑ አስረድተዋል:: በመጨረሻም፤ አንድ ወይም ሌላ አይነት ከግብርና ውጭ የሆነ የስራ ልምድና የአስተዳደር ችሎታ፤ የማቀድና መሰረታዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ልምድ ምንጭ እንደሆኑ ጥናቱ አመልክቷል::ሞዴል አርሶአደሮች ተሰማርተው ልምድ የቀሰሙባቸውን ከግብርና ውጭ የሆኑ ስራዎችንም በተመለከተ ፤የንግድ ስራና በአካባቢ አሰተዳደር ውስጥ የተደረጉ ተሳትፎዎች ጥቂቶቹ ናቸው::

***አካባቢያዊ ሁኔታዎች፡-*** የሞዴል አርሶአደሮች ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (የአንተርፕረነርሺፕ) እንቅስቃሴዎች ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ከሚያሳድሩ አካባቢያዊ ሁኔታዎች መካከል የማህበረሰብ አመለካከት የመጀመሪያው ነው:: ከሞዴል አርሶ አደሮችና ከሌሎች የማህበረሰብ አባላት ጋር በተደረጉ ቃለመጠይቆች እንደታየው ጠንካራ ሰራተኞችን የሚያበረታታና የሚያደንቅ እንዲሁም እንደ ምሳሌ የሚቆጥር ማህበረሰባዊ አመለካከት መኖሩ ለሞዴል አርሶ አደሮች ስኬት ወሳኝ መሰረት ነው:: በሌላ ወገንም፤ ይህ ስኬት ከላይ ለተጠቀሰው አይነት አመለካከት የበለጠ መጎልበት እንደጠቀመ ታይቷል:: የማህበራዊ ግንኙነት ትስስሮችም እንዲሁ ለሞዴል አርሶ አደሮች ስኬት በእጅጉ ጠቃሚ ሆነው የተገኙ ሲሆን፤ በተለይም ጓደኞችና ዘመዶች በንግድም ሆነ በሌላ ስራ መጀመሪያ ላይ የመነሻ ካፒታል በመስጠት/በማበደር፤ ምክር በመለገስ፤ መረጃ በማቀበል እንዲሁም እንደ አርአያ በማገልገል ለሞዴል አርሶ አደሮች ውጤታማነት የበኩላቸውን እገዛ አድርገዋል::

የተሻለ የገንዘብ አቅርቦት ማግኘት ሞዴል አርሶአደሮች በተለያዩ ስራዎች እንዲሰማሩ ብሎም ውጤታማ እንዲሆኑ ከረዱ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ውስጥ ሁለተኛው ነው:: የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ዋነኛው የብድር ምንጭ ሲሆን ቃለመጠይቅ ከተደረገላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ውስጥ አብዛኞቹ ለግብርና ስራዎችና ከግብርና ውጭ ላሉ ስራዎች ብደር ተበድረው ተጠቅመዋል፤ እየተጠቀሙም ይገኛሉ:: ጥናቱ በተካሄደበት ወረዳ የሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራትም (በተለይም 13 የብድርና ቁጠባ ማህበራትና አንድ የአድላቢዎች ማህበር) ብድር በማቅረብና ከሌላ አካላት የሚገኙ ብድሮችን በማስተዳደር የጎላ ሚና አላቸው::

የእርሻ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የአርሶአደሮችን ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (የአንተርፕረነርሺፕ) እንቅስቃሴዎች የሚደግፍ መሆኑን ለማወቅ ጥናቱ የሞከረ ሲሆን፤ ሞዴል አርሶአደሮች የእርሻ ኤክስቴንሽንን በሰፊው እንደሚጠቀሙ፤ በዚህም የተነሳ ስኬታማ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል:: በየቀበሌዎቹ የሚገኙት የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ከአርሶአደሩ ጋር በቅርበት የሚሰሩ ሲሆን ከእነኚህ ውስጥ ልዩ ችሎታና ትጋት ያላቸው ለሞዴል አርሶአደሮች ስኬት ያደረጉት አስተዋጽኦ ተደጋግሞ ተነስቷል:: የእርሻ ኤክስቴንሽኑ ዋና አካል የሆኑት የገበሬ ማሰልጠኛዎችም አርሶአደሮች ገበያ-ተኮር ምርት እንዲያመርቱና ውጤታማ ወደሆኑ የግብርና ስራዎች (ንብ ዕርባታ፣ዶሮ ዕርባታ የመሳሰሉት) በስፋት እንዲገቡ በማሰልጠንና በመገፋፋት በተለይም የስልጠናው ዋና ተሳታፊ የሆኑት ሞዴል አርሶአደሮች ውጤታማ እንዲሆኑ የበኩላቸውን

ሚና ተጫውተዋል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ምንም እንኳ ከአርሶአደሮች ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ ሥራ (አንተርፐረነር ሺፕ) ጋር የቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ባይመስልም የአርሶ አደሩንና የቤተሰቡን የጤና ሁኔታ በማሻሻልና ጤናማ የሰው ሀይል እንዲኖር በማድረግ በጎ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሞዴል አርሶአደሮች ለስኬታቸው ምክንያት አድርገው ካቀረቧቸው ጉዳዮች መካከል የህብረት ስራ ማህበራት ይገኙበታል፡፡ በጥናቱ ወረዳ በተለያዩ የስራ ዘርፎች የተሰማሩ 30 ያህል የህብረት ስራ ማህበራት ሲኖሩ በጥናቱ የተካተቱት ሞዴል አርሶደሮች በነኝህ ማህበራት አባል ነታቸው (ጥቂቶቹም በመስራች አባልነታቸው) ምክንያት ከፍተኛ ጥቅም ማግኘታቸውን ይገልጻሉ፡፡ የቁጠባ ልምድ፣ የብድር አቅርቦት፣ የግብአት አቅርቦት፣ የገበያ መረጃ እንዲሁም ምርታቸውን በነጋዴ ሳይታለሉ የመሸጥ እድል በህብረት ስራ ማህበራት አባልነታቸው ካገኙዋቸው ጥቅሞች መካከል ይገኛሉ፡፡

ሞዴል አርሶአደሮች አምርተው ለመበልፀግ እንዲጥሩ ብሎም እንዲሳካላቸው ከረዱዋቸው ነገሮች ውስጥ የአካባቢ ሰላምና ደህንነት መኖር አንዱ ነው፡፡ በተለይም ባለፈው የመንግስት ስርአት ወቅት የነበረውን የሰላምና ደህንነት እጦት ሁኔታ እንደ ምሳሌ በማንሳት በአሁኑ ግዜ የፈለጉትን አምርተው በፈለጉት ጊዜና ቦታ በገበያ ዋጋ ለመሸጥ መቻላቸው እንዲሁም የተሻለ አካባቢያዊ ደህንነት መኖሩ የአርሶአደሮችን ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (አንተርፐረነርሺፕ) እንቅስቃሴዎች የሚያበረታቱ ሁኔታዎች እንደሆኑ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሞዴል አርሶአደሮችና ሌሎች የማህበረሰብ አባላት አስረድተዋል፡፡

ከነዚህ በአካባቢ ደረጃ ከሚገኙ ሁኔታዎች ባለፈ ደግሞ ሀገር አቀፍ ፕሮጀክቶች ለሞዴል አርሶአደሮች ስኬት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ጥናቱ ተገንዝቧል፡፡ ከነኚህ ውስጥ የጥናቱን ወረዳ ጨምሮ በ23 የክልሉ ወረዳዎች የሚካሄደው የገጠር አቅም ግንባታ ፕሮጀክት አንዱ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ለግብርና ባለሙያዎች ሥልጠና የሚሰጥ ሲሆን በጥናቱ ወረዳ ለሚገኙት 17 የገበሬ ማሰልጠኛዎችም ድጋፍ አድርጓል፡፡ ሁለተኛው ፕሮጀክት "የኢትዮጵያ ገበሬዎች ምርታማነትና የገበያ ስኬት" ("Improving Productivity & Market Success (IPMS) of Ethiopian Farmers") የሚባለው ሲሆን፣ ለወረዳው የገበሬ ማሰልጠኛዎችም ድጋፍ ከማድረግ አልፎ ሞዴል አርሶአደሮች የተሰማሩባቸውን ግብርና ነክ ስራዎች በማገዝ ከፍተኛ የሆነ ሚና ይጫወታል፡፡

በመጨረሻም፣ ጥናቱ ሞዴል አርሶአደሮች ስኬታማ የሆኑት በእርሻ መሬቶቻቸው ስፋት፣ለምነት ወይንም ምቹነት መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የሞከረ ሲሆን፣ የተገኘውም ውጤት የሚያሳየው ሞዴል አርሶአደሮች የመሬት ይዞታቸው ስፋት (የኪራይ መሬትን ሳይጨምር) በለምነት ወይንም በምቹነት በአካባቢያቸው ካሉ ሌሎች አርሶአደሮች ጋር ተመጣጣኝ እንደሆነ፣ የመሬት ለምነት ልዩነት ቢኖርም እንኳ ሞዴል አርሶአደሮቹ እራሳቸው በሰሩዋቸው የማሳ እንክብካቤ ስራዎች እንደሆነ ነው፡፡

## የሞዴል አርሶአደሮች ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ እርምጃዎች፣ የገጠሟቸው እንቅፋቶችና የወደፊት እቅዶች

***ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ እርምጃዎች፡-*** በአንደኝነት በዚህ ወስጥ የሚካተቱት እርምጃዎች ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም ወጭን ለመቀነስ የተወሰዱት ሲሆኑ፣ እነዚህም ምርጥ ዘር መጠቀም፣ የኬሚካል ማዳበሪያ መጠቀም፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ማዘጋጀትና መጠቀም፣ የውሃ ፓምፖችን መጠቀም፣ ሳያርሱ መዝራት፣ ጥቁር አፈር ማጠንፈፍና ተጨማሪ መሬት መከራየት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የእርሻ ስራዎችን በአይነት ማስፋት ሁለተኛው እርምጃ ሲሆን፣ በርበሬና ሰሊጥ ማምረት፣የውሃ ፓምፖችን መጠቀም፣ አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት፣ እንዲሁም በበቆሎ ምርጥ ዘር ብዜት ላይ መሳተፍ በጥናቱ ቦታዎች የታዩ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡

በሶስተኝነት የምናገኛቸው እርምጃዎች የጎንዮሽ የእርሻ ስራዎችን በአይነት ማስፋት በሚል ሊጠቃለሉ የሚችሉ ሲሆን በጥናቱ ከተለዩት ውስጥ ዋናዎቹ የከብትና የበግ ማድለብ ስራ ሲሆኑ፣ ጌሾና ባህርዛፍ መትከል፣ የባህርዛፍ ችግኝ ማፍላትና መሸጥ፣ እንዲሁም ዶሮና ንብ ዕርባታ እዚሁ የሚካተቱ ናቸው፡፡ በመጨረሻም ከግብርና ውጭ ያሉ የስራ እንቅስቃሴዎችን እናገኛለን፡፡ በጥናቱ ቀበሌዎች አካባቢ በሚገኙ የገበያ/የመንገድ ዳር ከተሞች፣ በወረዳው ከተማ፣ አልፎ ተርፎም በክልሉ ዋና ከተማ፣ የሚከራዩ መኖሪያ ቤቶችን መገንባት፣ የበቅሎ ጋሪዎችን መግዛትና በስራ ላይ ማሰማራት እንዲሁም በጅምላ እህል ንግድ መሳተፍ ጥናቱ ያገኛቸው ከግብርና ውጭ ያሉ የስራ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ እነኚህም፣ አዋጭነታቸው ከፍ ያለ፣ በተለይም በጅምላ እህል ንግድ መሰማራት ደግሞ የብዙዎች ምኞት ሆኖ ታይቷል፡፡

***የሞዴል አርሶአደሮች ስኬት ለድህነት ቅነሳ ያለው አስተዋጽዖ፡-*** የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያሳዩት የሞዴል አርሶአደሮች ስኬት ከራሳቸውና ከቤተሰባቸው አልፎ ፣ለአካባቢያቸው ሳይቀር እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ነው፡፡ ድህነት ቅነሳን በተመለከተ፣ ሞዴል አርሶአደሮች በምግብ እህል ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለዋል፣ ገበያ ተኮር ምርቶችንም በማምረት ገቢያቸውን አሳድገዋል፡፡ የልጆቻቸውን የትምህርት ወጭ ለመሸፈን የቻሉ ሲሆን አንዳንዶቹም ልጆቻቸውን ወደከተማ በመላክ በግል ኮሌጆች ከፍለው ለማስተማር ችለዋል፡፡ እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ የጤና አገልግሎቶችን ከፍለው ለመጠቀም ችለዋል፡፡ ከዚህም በላይ አንዳንድ ሞዴል አርሶአደሮች በግብርና ላይ በሰፊው በመሰማራታቸው ከቤተሰባቸው ውጭ የጉልበት ሰራተኞችን ለአጭርና ረዥም ጊዜ ቀጥረው ያሰራሉ፡፡

***እንቅፋቶች፡-*** ጥናቱ ከለያቸው እንቅፋቶች ውስጥ ከአካባቢ ጋር የተያያዘው የዝናብ መጠንና ጊዜ የመለዋወጥ ችግር አንዱ ሲሆን፣ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖሊሲ-ነክ የሆኑት ደግሞ ላመረቱት ምርት አስተማማኝ ገበያ በበቂ ያለመገኘት፣ የእርሻ መሬት እጥረት፣ የፋይናንስ እጥረት፣ እንዲሁም አስተማማኝ ያልሆነ የግብርና ኤክስቴንሽን ግብአቶች አቅርቦት ችግር ደግሞ ሌሎቹ ናቸው፡፡

***የወደፊት እቅዶች፡-*** የሞዴል አርሶአደሮችን የወደፊት እቅዶች በተመለከተ በአንድ ወገን፣ ግብርና ውስጥ እንዳሉ ምርትን መጨመርን አላማ አድርገው የያዙ ሲኖሩ በሌላ ወገን ደግሞ ከግብርና ውጭ ያሉ ስራዎች ላይ ለማተኮር የሚፈልጉ አርሶአደሮች ተገኝተዋል፡፡ አብዛኞቹ በጥናቱ የተካተቱ ሞዴል አርሶአደሮች ግን ወደ ግብርናው ያዘነብላሉ፡፡

## ሞዴል አርሶአደሮች በሌሎች የማህበረሰብ አባላት አይን

በጥናቱ ቀበሌዎች ከሚገኙ የማህበረሰብ አባላት ጋር በተደረጉ ቃለመጠይቆችና የቡድን ውይይቶች እንደተደረሰበት፣ ሞዴል አርሶአደሮች በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን፣ውጤታቸውም ጠንክሮ ከመስራት የመነጨ ተደርጎ የሚወሰድ፣ እነሱም እንደ አርአያ የሚታዩ ናቸው፡፡ ከዚህም አልፎ፣ ሞዴል አርሶአደሮች በማህበረሰቡ ጉዳዮች ውስጥ ሰፊና ገንቢ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

በተጨማሪም፣ ሞዴል አርሶአደሮች ከእነርሱ ጋር ኩታ-

ገጠም ማሳ ያላቸውን ሌሎች አርሶአደሮችና በልማት ቡድን ውስጥ ከእነርሱ ጋር/በእነርሱ ስር ያሉ አርሶአደሮችን በማገዝና እውቀታቸውንና ልምዳቸውን በማጋራት በማህበረሰቡ ውስጥ ጠቃሚ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ::

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች

የዚህ ጥናት ዋና ጭብጥ ጥናቱ በተካሄደባቸው ሦስት ቀበሌ ዎች ሞዴል አርሶ አደሮች የተለያዩ ምርትና ገቢ ማስገኛ መንገዶችን በስፋት በማካሄድ የራሳቸውንም ሆነ የቤተሰባቸውን ኑሮ ለማሻሻል ደፋ ቀና እያሉ መሆኑ ነው:: ለምሳሌ ምርት ለመጨመር በስፋት መሬት መከራየት፣ የተለያዩ ገቢዎችን የሚያስገኙ ሰብሎችን ማምረት፣ እንዲሁም ከግብርና ውጭ መጠነኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች ማድረግና በቁጠባ ገንዘባቸውን በማስቀመጥና ከተቀማጭ ሂሳብ ወለድ በማግኘት፣ አስፈላጊም ሲሆን ብድር በመበደር የፋይናንስ አቅማቸውን በማጐልበት ላይ ናቸው::

ሞዴል አርሶአደሮች ከሚያሳዩአቸው አበረታችና ጠንካራ ጐኖች መካከል ለለውጥ መነሳሳት፣ ኑሮን ለማሸነፍ መጣር፣ አዳዲስ ገቢ ማስገኛ መንገዶችን መጠቀም፣ የግብርና ሥራቸውን በእቅድ ለመምራት መሞከር፣ የኤክስቴንሽን ግብአቶችን በልማት ሠራተኛ ምክር መሠረት መጠቀም፣ ከልማት ሠራተኞች ጋር በአዳዲስ ግብርና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ ጥሩ ግንኙነት መመሥረት፣ ሌሎች አርሶ አደሮችን ለመርዳት ፈቃደኛ መሆንና ውጤት ያስገኛሉ የሚባሉ ሥራዎችን የመፈተሽ ዝንባሌ ማሳየት ናቸው:: ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ሰፋ ባሉ ኢንቨስትሜንት ዘርፎች በግብርና ወይም ከግብርና ውጭ ለመሳተፍ ፍላጐት ቢያሳዩም ጠቀም ያለ ብድር ባለማግኘታቸው ከፍተኛ መሰናክል ሆኖባቸዋል::

ሞዴል አርሶአደሮች በአሁኑ ወቅት የሚያሳዩአቸው ከግብርና ጋር የተያያዙ አበረታችና ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸውና እነዚህም ተመክሮዎች ለሌሎች አርሶአደሮች የሚኖራቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ (በተለይም ድህነትን ከመቀነስ አንፃር) ለማጠናከር የሚከተሉት ዋና ዋና የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል:-

1. ሞዴል አርሶአደሮች መደበኛ ትምህርት መቅሰማቸው የጠቀማቸው መሆኑን ያመለከቱ ሲሆን ይህም እንዲጠናከር ትምህርትን ለአርሶአደሩ ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት በስፋት መቀጠል ይገባዋል::
2. ቀደም ሲል በቀበሌ አስተዳደር፣ በውትድርና እንዲሁም ከጠንካራ አርሶ አደሮች ዘንድ ተቀጥሮ በመስራት ልምድ ያገኙ ሞዴል አርሶአደሮች ውጤታማ መሆናቸውን ገልፀዋል:: ስለዚህ በተቻለ መጠን አርሶአደሮች ልምድ የሚያገኙበት ሁኔታ ከቀበሌም አልፎ በወረዳ ደረጃ መበረታታት አለበት::
3. የአርሶአደር ማሠልጠኛ ጣቢያዎች የአርሶአደሮችን ክህሎት ለማገጎልበት ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ ቢሆንም ለአብዛኞቹ የውስጥ ቁሳቁስ (መማሪያ ክፍል፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ) ያልተሟላ በመሆኑ የማሠልጠን ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት አልቻሉም:: ስለሆነም እነዚህ ማዕከላት ተልእኳቸውን በአግባቡ እንዲወጡና የአርሶ አደሩ የዕውቀት ማዕከላት መሆን እንዲችሉ በቂ የበጀትና የባለሙያ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል::
4. ሞዴል አርሶ አደሮች በሚሰጡት ድጋፍ የተነሳ ሌሎች አርሶ አደሮች የመነቃቃትና ከማን አንሼ ስሜት እየተፈጠ ረባቸው ነው:: ለዚህም ተጎራባች አርሶአደሮችን በአምስት-ለአንድ የማደራጀቱ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ደጋፊ አርሶ አደሮች ያላቸውን ተሞክሮና ክህሎት በቀጣይ ለሌሎቹ እንዲያጋሩ የማድረግ ሥራ መሠራት አለበት::
5. የልማት ሠራተኞች በተለይም ለሞዴል አርሶ አደሮች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ነው:: ይሁን እንጂ በቁጥር የሚበዛው ሞዴል ያልሆነው አርሶ አደርም ሙያዊ ድጋፍ ከልማት ሠራተኛው ይፈልጋል:: ይህን አገልግሎት በተሻለ ለመስጠት ይችሉ ዘንድ ለልማት ሠራተኞች የተለያዩ ድጋፎች (ለምሳሌ በቂ በጀት፣ ቁሳቁስ፣ ሥልጠናና ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ትራንስፖርት) ቢደረጉላቸው በተሻለ ሥራቸውን ሊሠሩ ይችላሉ::
6. ጥናቱ በተካሄደባቸው ቀበሌዎች የተወሰኑ የገጠር ከተሞች (ለምሳሌ ቁጭ በዝየው ሸውን፣ ፈጣም በፈጣም ሰንቶም) የንግድ ልውውጥ ማዕከል በመሆን በየአካባቢያቸው ለሚኖሩ አርሶ አደሮች የገበያ/ቢዝነስ አገልግሎት የመስጠት አቅም አላቸው:: ይህ እውን የሚሆነው ግን በማቆጥቆጥ ላይ ያሉ እነዚህን መሰል ከተሞች በመሠረተ ልማት (ማለትም መንገድ፣ የተጠናከረ የምርት ግብይት፣ የብድር/ባንክ አገልግሎት፣ ጠንካራ የከተማ ልማት፣ የመብራት ኃይል አቅርቦት) ሲጠናከሩ ነው:: ለዚህም መንግስት ትኩ ረት ቢሰጥ ጥሩ ነው::
7. ሁሉም አርሶ አደሮች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (የአንተርፕረነርሺፕ) እንቅስቃሴዎች የሚያካሄዱ ቢሆንም ባለው ስነምህዳራዊ (የአግሮ ኢኮሎጂ) ሁኔታ ይወሰናሉ:: ስለዚህ በተለያዩ አካባቢ የሚኖሩ አርሶ አደሮች እንደ ስነምህዳራዊው ሁኔታቸው በአካባቢው አዋጭ ሊሆኑ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ የፈጠራ (የአንተርፕረነርሺፕ) እንቅስቃሴ (ለምሳሌ በግ ማድለብና ባህር ዛፍ ማልማት በደጋ፣ የፍራፍሬ ልማት በወይና ደጋና በቆላ) በማጠናከር አርሶ አደሮች የተለያዩ ገቢ ማስገኛ መንገዶችን እንዲያዳብሩ ከልማት ሠራተኞች ሙያዊ ድጋፍ በተጠናከረ ሁኔታ ማግኘት አለባቸው::


**አበጀ ብርሀኑ (ዶ/ር)**

**ኢዛና አምደወርቅ (አቶ)**



**ምንጭ**:- Abeje Berhanu and Ezana Amdework. 2010. *“Peasant Entrepreneurship and Rural Poverty Reduction: The Case of Model Farmers in Bure Wereda, West Gojjam Zone”* a study commissioned by Forum for Social Studies (FSS), Addis Ababa. The researchers are faculty members of the Department of Sociology, Addis Ababa University (AAU).



ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በለጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲያኑ ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም::



አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

❄ **ስልክ** 011-629 78 88/91 ❄ **ፋክስ** 011-629 78 89 ❄ **ኢሜይል**: fss@ethionet.et ❄ **ድረ-ገፅ** www.fssethiopia.org.et